# ነገረ ጥምቀት/ Baptism

ባለፉት ጊዚያት ብዙ ያጋጠሙኝ ሰዎች የ Baptistን denomination ጥምቀት ያድናል ፣ ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት ይሆናል ብለን እንደምናምን አድርገው እንደሚያስቡ አስተውያለው ። ይህ ግን እጅግ ስህተት ነው ! "ታዲያ ጥምቀት ያድናል ብላችሁ የማታምኑ ከሆነ ለምን Baptist ተባላችሁ" ብለው ብዙዎች ይጠይቃሉ ። እኛ መጥሙቃዊያን የተባልንበት ዋና ምክንያት Credo-baptism ስለምንቀበል እና Pedo-baptismን ስለማንቀበል ነው ባፕቲስት የተባልነው እንጂ ፈፅሞ ከድነት ከኃጢአት ይቅርታ ጋር ተያይዞ መቅረቡን አናምንም ።

በዚህ ተከታታይ ትምህርት በዋናነት የምንመለከታቸው የካቶሊክ የነገረ ጥምቀት ምልከታ ፣ የ Reformers የጥምቀት ምልከታ ፣ ጥምቀት ለድነት ወይንስ የዳነ ሰው ነው ሚጠመቀው ? ፣ ጥምቀት ለኃጢአት ይቅርታና ለዳግም ልደት ይሆናል ? ፣ ማን ይጠመቅ ? (Subjects of Baptism) ፣ እንዴት እንጠመቅ ? (Mode of Baptism) ፣ በማን ስም እንጠመቅ? የሚሉትን ይሆናል ።

## ጥምቀት ያን ያህል ለምን አስፈላጊ ሆነ ?

አብዛኛው ጊዜ የምናደርገውን ነገር ለምን እንደምናደርግ አናውቅም ። ብዙ ጊዜ አንድ ነገር ሲደረግ ስለነበር ብቻ ነው የምናደርገው እንጂ ስለገባን አይመስለኝም ። ይህ ማለት አንድ ነገር ሲደረግ ስለነበር መደረጉ በራሱ ስህተት ነው ማለት አይደለም ። ምክንያቱም የሆነ ነገር ሲደረግ ያለ ምክንያት አይደረግም ስለዚህ የሚደረግበትን ምክንያት ማወቅ አለብን ማለቴ ነው ።

ምክኒያቶቹ እንደሚከተሉት ናቸው ፦ ፩ኛ, ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ – ማቴዎስ ፫ (አዲሱ መ.ት) ። ፲፫ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ፲፬ ዮሐንስ ግን፣ "ይህማ አይሆንም፤ እኔ ባንተ መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ?" ብሎ ተከላከለ። ፲፭ ኢየሱስም፣ "ግድ የለም ፍቀድልኝ፤ ይህን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና" አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ። ፲፮ ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው ወጣ፤ ወዲያውኑም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ። ፲፯ እነሆ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።

እንደሚታወቀው ዮሐንስ የመመያጠምቀው ለኃጢአት ስርየት ነው ። ታዲያ ጌታ ኢየሱስ የተጠመቀው ኃጢአተኛ ስለሆና ከኃጢአቱ ንስሃ እየገባ ነው ? ይህ በፍፁም ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም ቅዱሳት መፅሐፍት የሚናገሩት ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት መሆኑ ነው ። ታዲያ ኃጢአተኛ ካልሆነና ለኃጢአቱ ንስሃ እየገባ ካልሆነ ለምን ተጠመቀ ? በርካታ ምክንያቶችን መመልከት እንችላለን ። በእዚህኛው ክፍል ቢያንስ አምስት ምክንያቶችን እንመልከት ፦

፩ኛ, ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ። የኢየሱስ ጥምቀት ለእግዚአብሔር ታዛዥ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። ምንም እንኳን እሱ ንስሃ መግባት ወይም የኃጢአት ስርየት ባያስፈልገውም ኢየሱስ በመጠመቁ ራሱን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አስማምቷል ። ለእግዚአብሔር ዓላማ በመገዛትን ትሕትናን አሳይቷል። ይህ ድርጊቱ እንደ መሲህ ያለውን ሚና የማረጋገጥ ነው ።

፪ኛ, በመጠመቅ ለህዝቡ ወኪል በመሆኑ ከህዝቡ ጋር እራሱን Identity እያደረገ ነው ።

፫ኛ, አገልግሎቱን በይፋ ለመጀመር

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ሰማያት ተከፈቱ ፣ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ ፣ የእግዚአብሔርም ድምፅ "የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ በእርሱ ደስ ይለኛል" የሚል ድምፅ ከአብ *Acknowledgment* ሲመጣ እንመለከታለን ። ይህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እና መሲሕ መሆኑን አረጋግጧል ። በእዚህም ጥምቀቱ ምድራዊ አገልግሎቱ በአደባባይ መጀመሩን የሚያመለክት ነው ።

፥ኛ, ለአማኞች ምሳሌ ለመሆን ።

የኢየሱስ ጥምቀት ክርስቲያኖች ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ሆኗል ። የኢየሱስ የጥምቀት ድርጊቱ የጥምቀትን አስፈላጊነት በተከታዮቹ ሕይወት ውስጥ ሊኖር እንደሚገባው ስፍራ አሳይቷል። የኢየሱስን የጥምቀት ስረአት መፈፀሙ ይህም ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ እና የመገዛት ተግባር ነው ። በዚህ መንገድ የእርሱ መጠመቅ ለሚከተሉት ሰዎች መንፈሳዊ ተግባር አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

፭ኛ, የዮሐንስን አገልግሎት ለማረጋገጥ ። ኢየሱስ በዮሐንስ በመጠመቁ የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጧል። የዮሐንስ ሚና የመሲሑን መንገድ ማዘጋጀት ፣ ሰዎችን ወደ ንስሐ በመጥራት እና የሚመጣውን አዳኝ መጠቆም ነበር ። ኢየሱስ ለዮሐንስ ጥምቀት መገዛቱ የዮሐንስን ትንቢታዊ ሚና አረጋግጧል።

፪ኛ, በጌታ በራሱ የተደነገገ ስለሆነ ። – ማቴዎስ ፳፰ (አዲሱ መ.ት) ። [፲፱] ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ [፳] ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" በእዚህ በዋናነት ሁለት ነገር መመልከት እንችላለን ። ፩ኛ, ጥምቀት የማይሻር እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ የሚዘልቅ ቅዱስ ስርአት መሆኑንን ። ይህንን እንዴት እንረዳለን ኢየሱስ ፈፅሙ ያላቸውን ትዕዛዝ የሚፈፅሙ ከሆነ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር ለመሆ ቃል በመግባቱ ጥምቀት እና ከእርሱ ጋር ጎን ለጎን የቀረቡት ትዕዛዞች እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ የሚዘልቁ መሆናቸውን እንመለከታለን ። ፪ኛ, ጥምቀት የጌታ ታላቅ ሀደራ መሆኑን እንመለከታለን ። ይህንን እንዴት እንረዳለን ? ለምሳሌ አንድ ወዳጅ በአካል ከቤተሰቡ ወይንም ከጓደኞቹ የሚለያቸው ከሆነ የመጨረሻ ቃላቶቹ እጅግ ወሳኝ ነው ። ኢየሱስም ከእነርሱ በአካል በሚለይበት ጊዜ የሰጣቸው አደራ ጉዳዩ ምን ያህል *Serious* እንደሆነ የሚያመለክት ነው ። በእዚህም ትዕዛዝ መሰረት ጥምቀት ደቀመዝሙር እንደሆንን የምንገልጥበት ሳይሆን ደቀመዝሙር መሆኛ መንገድ በመሆነ እጅግ ወሳኝ ያደርገዋል ።

፫ኛ, የሐዋርያት ስራ የመጀመሪያ ስብከትን ተከትሎ የተሰጠ መመሪያ ስለሆነ ። – ሐዋርያት ፪ (አዲሱ መ.ት) ።
[፴፯] ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው እጅግ ተነካ፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋርያት፣ "ወንድሞች ሆይ፤ ታዲያ ምን እናድርግ?" አሏቸው። [፴፰] ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ "ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። ይህ ከቤተክርስቲያን መመስረት ጋር ተያይዞ የቀረበ መመሪያ ነው ።

**፥ኛ, በቤተክርስቲያን ታሪክ ለመለያየት ምክንያት ስለሆነ** ጥምቀትን *seriously* እንድንመለከተው ያደርጋል። ማለትም በጣም አከራካሪ ሆኖ አብያተ ክርስቲያናትን ስለከፋፈለ ነገሩ በራሱ ከባድ እንደሆነና ትልቅ ስፍራ እንደተሰጠው የሚያመለክት ነው ። አንድ መሆን የእግዚአብሔር ሀሳብ ቢሆንም ነገርግን አንድ ነገር ልክ አይደሉም ብሎ እያመኑ ለተቋም አንድነት ሲባል አንድ መሆን እጅግ አደገኛ ነገር ነው ። የትምህርት ልዩነት ሲኖር መለያየት እጅግ ጤናማ ነገር ነው ።

## የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጥምቀትን በተመለከተ ያላት ምልከታ

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ቁርባን እና ጥምቀትን ለድነት አስፈላጊ ነገሮች  ናቸው ትላለች ። በጠቅላላው ጥምቀት ለመዳን ፣ ለዳግም ውልትና ለኃጢአት ስርየት ይሆናል ብላ ታምናለች ።  ደግሞም የሕፃናት ጥምቀት የመጀመሪያ ኃጢአትን ማለትም የውርስ ኃጢአትን ያስወግዳል ÷ ጥምቀት የቀደመውን ኃጢአት (ከአዳም የወረሱትን የወደቀውን የሰው ልጅ ተፈጥሮ) የሚያስወግድ የጸጋ መንገድ ተደርጎ ይታያል ።ማለትም (*baptismal regeneration*) ትቀበላለች ።

## የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የጥምቀት ዓይነቶች ፡-

በካቶሊክ ትምህርት ውስጥ ሦስት የታወቁ የጥምቀት ዓይነቶች አሉ። እነርሱም ፡-

1ኛ, የውሃ ጥምቀት ፡-  ይህ በቀጥታ ውሃ በሰውየው ላይ የሚፈስበት ካህኑ ወይም ዲያቆኑ  “በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቃችኋለሁ” ይላል። ይህ በጣም የተለመደው የጥምቀት ዓይነት ሰሰለሆነ ብዙም ማብራሪያ አያስፈልገውም ።

2ኛ,የምኞት ጥምቀት ፡- ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው ለመጠመቅ ቢፈልግ ነገር ግን ቅዱስ ቁርባንን ከመውሰዱ በፊት ቢሞት ። የመጠመቅ ፍላጎቱ በራሱ የመዳንን ጸጋ ያመጣል ይላሉ ።  ለምሳሌ ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለው ሰውዬ የሞተው ከመጠመቁ በፊት ነው ። ይህ ሰውዬ ለመጠመቅ እድሉን አላገኘም ነገር ግን የመጠመቅ ፍላጎቱ ስለነበረው የምኞት ጥምቀትን ተጠምቋል ይላሉ ።  ይህ ለእነርሱ የ ጥምቀት ለድነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመለክት ነው ።

3ኛ, የደም ጥምቀት ፡- ይህ የሚያመለክተው ከመጠመቃቸው በፊት ለእምነታቸው የሚሞቱትን እንደ ሰማዕታት ያሉ ግለሰቦችን የሚወክል ነው ። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን እንደዚህ አይነት ሰዎች የሚድኑት በሰማዕትነታቸው እንደሆነ ታስተምራለች ። ይህም ልክ እንደ ጥምቀት አይነት ህይወታቸውን ለክርስቶስ ለመስጠት በመፈለጋቸው ነው ።

## አንድ ሰው ከጥምቀት በኋላ ኃጢአት ከፈፀመስ ?

አስቀድመን የኃጢአት ይቅርታ የሚገኝበትን መንገድ ከማብራራታችን አስቀድሞ ካቶሊኮች ኃጢአትን የሚረዱበትን መንገድ እንመልከት ። በካቶሊክ ሥነ-መለኮት ውስጥ ኃጢአቶችን በሁለት ይከፈላሉ *Mortal Sins* እና  *Venial Sins* በመባል።

1ኛ, *Mortal Sins.* ይህ አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያፈርሱ በጣም ከባድ ጥፋቶች የሚያመለክት ነው ። *Mortal Sins* የሚባሉት ለምሳሌ፡- ግድያ ፣ ዝሙት ፣ *Blasphemy* ( እግዚአብሔር ያለ አክብሮት መናገር) ፣ ስርቆት (ትልቅ ወይም ትልቅ ዋጋ ያለው) እና **የሀሰት ምስክርነት** ናቸው ። አንድ ሰው *Mortal Sins* ቢሠራ የቅድስና እና ፅድቅን ማጣትን ያስከትላል ብለው ያምናሉ ።

2ኛ, *Venial Sins/* ይቅርታ የሚደረግለት ኃጢአት

እነዚህ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ህግ ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቅን ጥሰቶች ናቸው ብለው ያስተምራሉ ። *Venial*

Sins የሚባሉት ለምሳሌ፦ ስለ ጥቃቅን ጉዳዮች መዋሸት ( ምንም ጉዳት የሌላቸውን ውሸት መናገር) ፣ በትንሽ መንገድ ትዕግስት ማጣት ወይም ቁጣ ፣ ያለ ተንኮል ማማት ወዘተረፈ ። ጸጋን የሚያዳክሙ ቢሆንም የመቀደስን ወይንም ፅድቅን አያሳጡም ።

በእነዚህ መንገዶች ኃጢአት ቢሰሩም ነገር ግን ኃጢአታቸው የሚሰረይበት ሌላ መንገድ አለ ። እርሱም ***Penance*** ብለው ይጠሩታል ። ይህም ስረአት የሚፈፀምበት መንገድ እንደሚከተለው ነው ፦ ኃጢአቱን የሰራው ግለሰብ በግሉ ይፀፀታል ፣ ከእዚያም ለካህን ኃጢአቱን ይናዘዛል እናም ንስሐ ይገባል ። ለካህኑ በሚናዘዝበት ጊዜ ካህኑ ያዳምጣል ፣ ምክር ይሰጣል እናም መመሪያ ይሰጣል ። በስተመጨረሻ ካህኑ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ ወደተናዛዡ በመዞር “በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ከኃጢአት ነጻ አድርጌያለሁ” የሚለውን ቃላቱን ይናገራል። ካህኑ ሰውየውን ከኃጢአቱ ካነጻ በኋላ ለኃጢአቱ ማካካሻ ጸሎቶችን፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችን፣ ጾምን ወይም ሌሎች ድርጊቶችን የያዘ ንስሃ ይመድባሉ ። ይህ ግለሰቡ ለተፈፀመው ስህተት ለማረም ያለውን ፍላጎት ያሳያል። ለእዚህም ዋና መሳሪያ ቁርባን በመባል ይታወቃል። የዚህ ቅዱስ ቁርባን ዓላማ ግለሰቡ ከጥምቀት በኋላ ለፈጸሙት ኃጢአት ይቅርታን በመጠየቅ ከእግዚአብሔር እና ከቤተክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት መመለስ ነው።

## Reformers ጥምቀትን እንዴት ይመለከቱታል ?

*Reformers* ተብለው በዋናነት የሚታወቁት *John Calvin*, *Martin Luther*, *Ulrich Zwingli*, *Philipp Melanchthon* ናቸው ። የተሐድሶ አራማጆች ስለ ጥምቀት የተለያዩ አመለካከቶች ነበሯቸው ነገር ግን በአጠቃላይ በብዙ መሰረታዊ የክርስትና አስተምሮዎች ላይ እንደሚስማሙ ግልጽ ነው ። ደግሞም ጥምቀት ለክርስቲያናዊ ሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ በአንድነት ይስማማሉ ። ነገር ግን አቀራረባቸው ላይ ልዩነታቸውን ያንጸባርቃሉ ።

1ኛ, *Martin Luther* (ማርቲን ሉተር) (1483-1546)

ሉተር ጥምቀት ለዳግም መወለድ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይመለከተው ነበር። ሉተር ጥምቀት ከኃጢአት ስርየት ጋር በቅርበት የተቆራኘ መሆኑን አስተምሯል ። እንዲሁም (*means of grace*) ነው ብሎ ያምናል ። የግዴታ ባይሆንም ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊ መሆኑን ያምናል ። ጥምቀት ለድነት ይሆናል ሲል የእግዚአብሔር ሥራ እንጂ የሰዎች ሥራ አይደለም ብሎም ያምናል ። ሉተር የሕፃን ጥምቀትን አጥብቆ ይደግፈዋል እናም ልጆች ወደ ቃል ኪዳኑ ለመግባት እና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት መጠመቅ አስፈላጊ እንደሆነ ያምን ነበር።

2ኛ, *Philipp Melanchthon* (ፊሊፕ ሜላንክተን) (1497-1560)

ፊሊፕ ሜላንክተን የማርቲን ሉተር የቅርብ ጋደኛ የነበር ሰው ነው ።የሜላንክተን አመለካከት ከሉተር ጋር የሚስማማ ነበር ። ጥምቀት እግዚአብሔር የኃጢአትን ስርየት የሚሰጥበት መንገድ ተደርጎ ይታይ ነበር። *Melanchthon* ጥምቀት ምልክት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ጸጋን የሠራበት እውነተኛ መንገድ (*means of grace*)ነው ብሎ ያምናል ። *Melanchthon* ልክ እንደ ሉተር የሕፃን ጥምቀትን ጠንካራ ደጋፊ ነበር እናም እንደ ቤተ ክርስቲያን የቃል ኪዳን አካል አድርጎ ይመለከተው ነበር። ለእርሱ፣ ሕጻናት በቃል ኪዳኑ ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲካተቱ የሕፃናት ጥምቀት አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል ።

3ኛ, *John Calvin* (ጆን ካልቪን) (1509-1564)

ጆን ካልቪን ጥምቀት (*means of grace*) ነው ለሚለው በጣም ከፍ ያለ ትኩረት ሰጥቷል ። ነገር ግን ጥምቀት በራሱ ግለሰቡን አያድሰውም ብሎ ያምናል ። ነገር ግን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ምልክት እና ማኅተም ነው ብሎ ያምናል ። ምስጢራቶቹ ማለትም ጥምቀትን እና የጌታ እራት በራሳቸው *Regeneration*ንን አይሰጡም ይላል ። ለካልቪን ጥምቀት በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ያለው የቃል ኪዳን ምልክት ፣ እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ማኅተም ይመለከተው ነበር ። ይህም በብሉይ ኪዳን ከነበረው ግርዛት ጋር ያመሳስለዋል ።

ካልቪን የሕፃናት ጥምቀትን አጥብቆ ደግፏል ። የአማኝ ወላጆች ልጆች የቃል ኪዳኑ ማኅበረሰብ አካል ናቸው ስለዚህም መጠመቅ አለባቸው በማለት ይሞግታል ። ሕፃናት ልክ እንደ አዋቂዎች የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተቀባዮች ናቸው ይላል ።

*4ኛ, Ulrich Zwingli* (ውልሪች ዝዊንግሊን) (*1484-1531*)

የስዊዘርላንድ ተሃድሶ መሪ *Ulrich Zwingli* ጥምቀት አንድ ሰው ለክርስቶስ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያመለክት ምሳሌያዊ ተግባር ነው ብሎ ያምን ነበር ። ጥምቀት ራሱ ጸጋን ወይም ድነትን አይሰጥም ብሎ ያምናል ። ይልቁንም ጥምቀት የእምነት የአደባባይ መግለጫ ነው። ለዝዊንሊ፣ የመጠመቁ ድርጊት አንድ ሰው በክርስቶስ ላይ ያለውን እምነት የሚያሳይ ነው÷ የጥምቀት ትክክለኛ ጠቀሜታ ክርስቶስን ለመከተል ያለው ግላዊ ቁርጠኝነት ነው ብሎ ያምናል ። እንደ ሉተር እና ካልቪን ዝዊንግሊ የሕፃን ጥምቀትን አይቀበልም ። ጥምቀት መሰጠት ያለበት በግል እምነት ለሚናገሩ ብቻ እንደሆነ ያምናል። ጥምቀት ክርስቶስን የተቀበሉ እና አውቀው ወደ ሃይማኖት ለገቡ ሰዎች መሆን አለበት ይላል ። እነዚህ የተሀድሶ አባቶች ለጥምቀት ትልቅ ስፍራ የሚሰጡ መሆናቸውን እንመለከታለን ።

## በጥምቀት የኃጢአት ይቅርታ ይገኛል ?

በጣም ብዙ ሰዎች ኤፌሶን 4 ላይ በመመስረት ጥምቀት አንድ ነው ወይንም አንዲት ጥምቀት ብቻ አለ ይላሉ ። – ኤፌሶን 4፥5 (አዲሱ መ.ት) ። “አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤” ይህ ግን መፅሐፍ ቅዱስን በትክክል ካለማጥናት የመነጨ ድምዳሜ ነው ። ኤፌሶን ላይ አንዲት ጥምቀት ሲል ጥምቀት አንድ ብቻ ነው የሚለውን በአዕምሮአችን እንድናስብ አይደለም ።

አንድ የ *only Jesus* እምነት ተከታይ ስለ ጥምቀት እንድናወራ በአካል አጊኝቶኝ በቀጥታ ንግግሩን የጀመረው አንዲት ጥምቀት ስለሚል ያችን አንዲት ጥምቀት የምናስተምረውም የምናጠምቀው እኛ ነን አለኝ ። እኔም አንዲት ጥምቀት ብቻ ነው መጽሐፍ ይላል ወይ? አልኩት ÷ እርሱም አው አለኝ ። ከእዚያም እኔ ዕብራውያን ላይ ያለውን ጠቀስኩለት ። ዕብራውያን 6 (አዲሱ መ.ት) ። ¹ ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል፤ ² እንዲሁም ስለ ጥምቀቶች፣ እጆችን ስለ መጫን፣ ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ ትምህርት እንደ ገና አንመሥርት። ስለ ጥምቀቶች በማለቱ ጥምቀትን *plural* አድርጎ ገልፆታል ። ከእዚህ የተነሳ ሙግታችን እዚህ ጋር አበቃ ። ይህ አይነቱ ችግር አብዛኛው ጊዜ ስለ ጥምቀት ከሰዎች ጋር በሚወራበት ጊዜ ይገጥመኛል ።

*Almost* ማለት በሚባል ደረጃ ሁሉም ሰው ጥምቀት ሲባል ወደያው አዕምሮው ላይ ፈጥኖ የሚመጣው የውሀ ጥምቀት ነው ። መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአንድ በላይ የጥምቀት አይነቶችን እናያለን ። ብዙ ጥምቀቶች ካሉ አንዲት ጥምቀት ሲል ስለየትኛው ጥምቀት ብለን መጠየቅ አለብን እንጂ ጥምቀት አንድ ብቻ ነው ወደማለት አንሄድም ። ይህንን በቀጣዩ ክፍል ሰፋ አድርገን የምንመለከት ቢሆንም በጣም ብዙ ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስ

ጥምቀት ስላለ ብቻ ፈጥነው የውሃ ጥምቀት የሚያደርጉት ብዙ ሰዎች አሉ ። በብዛት ከውሃ ጥምቀት ጋር አያይዘውም ከሚተረጉሙት የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባብ መካከል አንዱ ቆላስይስ ላይ ያለው ነው ። – ቆላስይስ ፪ (አዲሱ መ.ት) ። ¹¹ በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ፤ ¹² በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፣ እርሱን ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር ኀይል በማመን ከእርሱ ጋር ደግሞ ተነሣችሁ። እዚህ ክፍል ላይ በጥንቃቄ ከተመለከትን መቀበር ይቀድማል ከዚያም ከሙታን መነሳት ይከተላል ። *Logically*ም የሚቀድመው መቀበር ነው ። ነገር ግን ጥምቀት የተያያዘው ከመቀበር ጋር ሲሆን እምነት ደግሞ የተያያዘው ከሙታን ከመነሳት ጋር ነው የተያያዘው ። ስለዚህ በእዚህ አተረጓጎም የውሃ ጥምቀት ነው የምንል ከሆነ ከዕምነት የሚቀድመው መጠመቅ ነው ማለት ነው ። ምክንያቱም መቀበረ በመጠመቅ የሚመጣ ሲሆን ከሙታን መነሳት ደግሞ ከእምነት ጋር ስለተያያዘ ። ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም አንድ ሰው ሳያምን ሊጠመቅ አይችልም ።

## ጥምቀት ወንጌል አይደለም ወይንም የወንጌል አካል አይደለም

በቤተ ዕምነቶች ደረጃ ጥምቀት ወንጌል እንደሆነና የወንጌል አካል ተደርጎ ይታሰባል ። ይህ ግን ስህተት ነው ። – ፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ (አዲሱ መ.ት) ። ¹³ ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ለእናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን? ¹⁴ ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በስተቀር ከእናንተ ማንንም ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤T¹⁵ ስለዚህ በስሜ መጠመቁን የሚናገር ማንም የለም። ¹⁶ በርግጥ የእስጢፋኖ ስንም ቤተ ሰው አጥምቄአለሁ፤ ከእነዚህ ሌላ ግን ማጥመቄ ትዝ አይለኝም። ¹⁷ <u>ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ</u> እንዳጠምቅ አይደለም፤ የክርስቶስም መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፣ በሰዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም። ወንጌሉ የክርስቶስ መስቀል ወይንም የመስቀሉ ቃል ነው ።

ደግሞም ምዕራፍ ፲፭ ላይ ወንጌሉ ምን እንደሆነ በጥልቀት ሲያብራራ ጥምቀትን አላካተተም ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ (አዲሱ መ.ት) ። ¹ አሁንም፣ ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክ ሁላችሁንና የተቀበላችሁትን ደግሞም ጸንታችሁ የቆማችሁበትን ወንጌል ላሳስባችሁ እወዳለሁ፤ ² የሰበክሁላችሁን ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ፣ በዚህ ወንጌል ትድናላችሁ፤ አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ ነው። ³ እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ የሆነውን ለእናንተ አስተላልፌአለሁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ⁴ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ⁵ ከዚያም ለኬፋ ታየ፤ ቀጥሎም ለዐሥራ ሁለቱ ታየ፤ ⁶ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ በላይ ለሚሆኑ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነዚህም አብዛኛዎቹ በሕይወት አሉ፤ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል። ⁷ ከዚያም ለያዕቆብ ታየ፤ በኋላም ለሐዋርያት በሙሉ ታየ፤ ⁸ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምቈጠር ለእኔ ደግሞ ታየ። በእዚህ ክፍል ስለወንጌል በእዚህ ጥልቀት እየነገረን ጥምቀት ወንጌል ከሆነ እንዴት ስለ ጥምቀት ሳያነሳ ይቀራል ?

ጥምቀትን እና የጌታ እራትን በተመለከተ በዋናነት የሚነሱ ሶስት ሀሳቦች አሉ ። *Ex opere operato*, ( ኦፔሬ ኦፔራቶ) ፣ *Ex opere operantis*(ኦፔሬ ኦፔራንቲስ) *and Ex opere Spiritus*( ኤክስ ኦፔሬ ስፕሪተስ) ። እነዚህ የላቲን ሀረጎች ናቸው ። በእነዚህ ሀረጎች የካቶሊኮችን የባፕቲስትንና የ *Presbyterian*ንን ምልከታዎች እንዳስሳለን ።

*፩ኛ, Ex opere operato*, ( ኤክስ ኦፔሬ ኦፔራቶ) ይህ የካቶሊክ ምልከታ ነው ። ሀሳቡም ፦ (*from the work working*) *efficacy* ያለው በሚያጠምቀው አካል ወይንም በተጠማቂው ቅድስና ሳይሆን የጥምቀት ስርአቱ በራሱ ከኃጢአት ያነፃዋል የሚል ነው ። ለምሳሌ፦ አንድ ካህን አንድን ሰው ቢያጠምቅ ምንም እንኳን ካህኑ በጸጋ

ሁኔታ ላይ ባይሆንም ወይም ተቀባዩ ለምን እንደሚጠመቅ ትርጉሙን ባያውቅም ። ጥምቀቱ በራሱ ሰውየውን ከኃጢአት የማጽዳት እና ወደ ቤተክርስቲያን የማስገባት ኃይል አለው ማለት ነው ።

ይህንን ስነመለኮት ያመጠበት ምክንያት ዶሊቲስቶች የሚባሉትን ለመቃወም ነበር ይህንን ስነመለኮት ያዋቀሩት ። እነዚህ አካላት የሚሉት እነዚህ ቅዱሳት ሚስጥራትን የሚሰጡ ቄሶች ቅዱስ ካልሆኑ ቅዱሳት ሚስጥራት ዋጋ የላቸውም የሚሉ ነበሩ ይህንን እኛም ሆነ ሌሎቹ ቤተ እምነቶች አይቀበሉም ።

2ኛ, *Ex opere operantis*(ኦፔሬ ኦፔራንቲስ) ይህ የባፕቲስት ምልከታ ነው ። ሀሳቡም ፦ (*from the worker working*) ማለትም ፦ *efficacy* ያለው በራሱ በጥምቀት ስርአቱ ሳይሆን በተጠማቂው እምነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ጥምቀቱ በራሱ የኃጢአት ይቅርታን አይሰጥም ። ይልቁንም የኃጢአት ይቅርታን የሚያገኘው በእምነቱ ነው ።

3ኛ, *Ex opere Spiritus*(ኦፔሬ ስፕሪተስ) ይህ *Presbyterian* አመለካከት ነው ። ሀሳቡም ፦ (*from the Sprit working*) *efficacy* ያለው መንፈስ ቅዱስ ጋር ነው ። የጥምቀት ስረአት ውጫዊ ሥነ ሥርዓት ቢሆንም ኃይሉ ያለው መንፈስ ቅዱስ ጋር ነው ። በጥምቀት ውስጥ የሚተላለፍ ጸጋ አለ ። ነገር ግን የጸጋው እውን የሚሆነው ስርአቱ ከሚፈፀምበት ጊዜ ጋር በቀጥታ የተያያዘ አይደለም። በእዚያው ጊዜ ከእዚያው በኃላ ሊሆን ይችላል ።

*Absolute necessity* የሚሉት ካቶሊኮች ናቸው ። ያለ ጥምቀት ሰው በጭራሽ አይድንም ፣ የኃጢአት ይቅርታን አያገኝም ፣ ደግም ውልደትን አያገኝም ይላሉ ። ይህ በ ፕሮቴስታንቱ አለም ተቀባይነት የለውም ። *ordinary necessity* ይህ በተለይም በ *Lutheran* የሚታወቅ ነው ። ድነትን እንቀበልበታለን ፣ ዳግሞ ልደትን እንቀበልበታለን ፣ የኃጢአት ይቅርታን እንቀበልበታለን ። ነገርግን በምንም መንገድ ከእዚህ ውጪ አይገኝም ማለት አይደለም ይላሉ ። ምክንያቱም ሰው ሳይጠመቅ ድኖ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለ ይላሉ ። በቀላሉ ነገሩን ለመረዳት ሰው በእምነት ብቻ ያለ ጥምቀት እና የጌታ እራት ይድናል ። ስለዚህ *Absolute necessity Faith* ነው ለ *Lutheran* ። ሰው ያለ እምነት አይድንም ። ያለ ቅዱሳት ሚስጥራት ግን ይድናል ብለው ያምናሉ ።

ከኃጢአት ይቅርታ ጋር ተያይዞ ሙግት የሚቀርብባቸውን ምንባባት እንመልከት ። — ሐዋርያት 2፥38 (አዲሱ መ.ት) ። “ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ “ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” ይህንን ክፍል በጥንቃቄ ካልተመለከትነው የኃጢአታችሁን ይቅርታ ለማግኘት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ እያለ ይመስላል ። የምርም ይህ ክፍል የኃጢአት ይቅርታ በጥምቀት ይገኛል እያለ ነው ? ይህንን በጥንቃቄ ለመመልከት እንሞክር ።

እዚህ ጋር ያለው ክርክር ***Eis*** የሚለው የግሪክ ቃል ነው ። ይህ ቃል በተለያየ መንገድ መፅሐፍ ቅዱሳችን ላይ ጥቅም ላይ ውሏል ። ነገር ግን እዚህ ክፍል ላይ እየተነሳ ያለው ክርክር *for* ተብሎ ነው መተርጎም ያለበት? ወይንስ *because of* ተብሎ ነው መተርጎም ያለብት? የሚል ነው ። በእርግጥ *for* የሚለው በራሱ ሁል ጊዜ አንድ አይነት ትርጉም አይኖረውም ። ነገር ግን ክፍሉን በጥንቃቄ ከተመለከትነው *because of* ተብሎ ነው መተርጎም ያለበት ። የኃጢአትን ይቅርታ ስላገኛችሁ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ እያለ ነው ። ይህንን ለመረዳት ምሁራን ምን አሉ የሚለውን አስቀድመን እንመልከትና ከእዚያም በማስከተል የመፅሐፉን ሀሳብ እንመለከታለን ።

*Eis* የምትለው የግሪክ ቃል በአዲስ ኪዳን 1774 ጊዜ ተጠቅሷል ። በአዲስ ኪዳን ካለው የቃሉ አጠቃቀም አንፃር

ሐዋሪያት ስራ 2:38 ላይ ያለው ቃል *because of* ተብሎ ነው መተርጎም ያለበት ይላሉ *A.T. Robertson, Charles Ryrie* እና *J.R. mantey* የሚባሉት ዕውቅ *Scholars.*

ለምሳሌ፦ ይህ ቃል *because of* ተብሎ ተተርጉመዋል ። — ማቴዎስ 12፥41 (አዲሱ መ.ት) ። "የነነዌ ሰዎች በፍርድ ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ ስብከት ንስሓ ገብተዋልና። እዚህ ጋር ***Eis*** የምትለው ቃል ***because*** ተብሎ ነው የተተረጎመው ። ይህ ክፍል በጣም ግልፅ ነው ። ንስሃ ስለገቡ የዮናስ ስብከት ተሰበከ ወይንም የዮናስ ስብከት ተከትሎ መጣ እያለ አይደለም ። እያለን ያለው በዮናስ ስብከት ምክንያት ንስሃ ገቡ ነው ። ይህ አገላለጽ ከሐዋሪያት ስራ 2:38 ምንባብ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ከእዚህ ምንባብ ተነስተን ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት አያስፈልግም ። ነገርግን ጥምቀት የኃጢአት ስርየት ያገኘንበት መገለጫ ስለሆነ ለእኛ ትልቅ ስፍራ አለው ።

**— ሌላኛው ሙግት**

የግሪኩ *Grammar* አወቃቀር የሚያመለክተው ቁጥር 2:38 ላይ ያለው ሁለት አረፍተ ነገር ነው እንጂ አንድ አይደለም ። አረፍተ ነገሩ ሁለት ከሆነ ደግሞ ኃጢአታቹ ይሰረይ ዘንድ የሚለው ማሰሪያ አንቀፅ ስለሆነ ተጠመቁ ወደሚለው ሊተላለፍ አይችልም ። ስለዚህ የግሪክ ሰዋሰውን መሰረት አድርገን ከተረጎምን የሚከተለውን ትርጉም ይሰጠናል ። ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ ። እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ። ይህ ነው የክፍሉ ውቅር ። ስለዚህ የኃጢአት ይቅርታ ያገኘ ሰው ነው የሚጠመቀው ።

የኃጢአት ስርየት ከንስሐ ጋር ተያይዞ እንዳቀረበ አንድ ምዕራፍ ስንሻገር እናገኛለን ። — ሐዋርያት 3፥19 (አዲሱ መ.ት) ። "እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል፤"

— ሌላኛው ጥምቀት ከኃጢአት ስርየት ጋር ተይዞ የሚቀርበው ሙግት — ሐዋርያት 22፥16 ላይ ያለው ሙግት ነው ። — ሐዋርያት 22፥16 (አዲሱ መ.ት) ። "ታዲያ፣ አሁን ምን ትጠብቃለህ? ተነሥተህ ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ።'" *FF Bruce* የተባለ ምሁር እንደሚለው ከሆነ የግሪኩ ሰዋሰው እንደሚያሳየን ከሆነ፦ አሁንስ ለምን ትዘገያለህ ? ተነሳና ተጠመቅ ፣ ስሙን እየጠራህ ከኃጢአትህ ታጠብ ። የሚል ይሆናል ይላል ። ስለዚህ የኃጢአት ይቅርታ የተያያዘው ከመጠመቁ ጋር ሳይሆን ስሙን ከመጥራት ጋር ነው የተያያዘው ።

ይህንን በተመለከተ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል ። ለምሳሌ ፦ — ሐዋርያት 10፥43 (አዲሱ መ.ት) ። "በእርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።""

— 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥11 (አዲሱ መ.ት) ። "ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።"

— 1ኛ ዮሐንስ 2፥12 (አዲሱ መ.ት) ። "ልጆች ሆይ፤ ኀጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና፣ እጽፍላችኋለሁ።"

*A.T. Robertson* እንደሚለው ከሆነ ፦ **የክፍሉን ሰዋሰው በትክክል የተረዳ ሰው የውሃ ጥምቀት የኃጢአት ስርየትንያስገኛል ለሚል ባዕድ ሀሳብ ይህንን ክፍል በማስረጃነት መጠቀም አይችልም** ። ስለዚህ ውሃ ውስጥ ገብቶ በመውጣት የኃጢአት ይቅርታን አገኛለሁ ማለት ኢ–መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው ። ከእዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ሰዎች *misrepresent* የሚያደርጉት ነገር ጥምቀት ለኃጢአት ይቅርታ ነው ሲባል ታዲያ ክርስቶስ ለምንን መሞት አስፈለገው እዛው ሰማይ እያለ በውሃ ተጠመቁ ማለት ብቻ አያስፈልገውም? ይላሉ ። ይህ ግን እነርሱ እያሉ

ያሉትን ካለመረዳት የሚመነጭ ነው ።

## የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው ?

በእዚህ ክፍል የሚጠመቀው ሰው የሚድን ሰው ነው ወይንስ የዳነ ሰው ነው ? ወይንም ለመዳን እንጠመቅ ወይንስ ስለዳንን እንጠመቅ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክራለን ።

የካቶሊክ ፣የኦርቶዶክስ እና እራሳቸውን የሐዋሪያት ቤተክርስቲያን ብለው የሚጠሩት ጥምቀት ለድነት የግድ አስፈላጊ ነው ይላሉ ። ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙትን የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት በጥንቃቄ ለመመልኩ እንሞክራለን ። ከሚጠቀሟቸው የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት መካከል አንደኛው ዮሐንስ ወንጌል ፫:፭ ላይ ያለው ነው ። በእርግጥም ዮሐንስ ፫:፭ ላይ ያለው ስለ ውሃ ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊነት ይናገራል ? የክፍሉን አውድና ከክፍሉ ጋር ተያይዞ የሚነሱ የተለያዩ ምልከታዎችን እንመልከት ።

– ዮሐንስ ፫፥፭ (አዲሱ መ.ት) ። “ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤”

ከውሃ የሚለው ላይ የተለያዩ ምልከታዎች

፩ኛ, ከውሃ የሚለው ጥምቀት ነው የሚሉ አሉ ።

ምናልባትም ቀጥሎ ከማቅረባቸው አማራጮች ውስጥ በጣም አደገኛ የሆነው የውሃ ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊ ነው የሚለው ነው ። ምክንያቱም ያለ ውሃ ጥምቀት ፈፅሞ ድነት አይገኝም የሚል ድምዳሜ ላይ ስለሚያደርሰን ። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም የሚለው ይህንን የሚያመለክት ነው ።

ይህ አስተሳሰብ ማለትም የውሃ ጥምቀት ነው የሚለው አስተሳሰብ ስህተት የሚሆንበት ምክንያት ቀጥሎ ባሉት በግልጽ ለማሳየት እሞክራለሁ ። ነገር ግን ይህንን ክፍል ስለ ውኃ ጥምቀት የሚናገር ነው ካልን አምነው ሳይጠመቁ የሞቱ ሁሉ ጠፍተዋል ማለት ነው ። ይህ ደግሞ የተሳሳተ አመለካከት ነው ። ከጠቅላላው የመፅሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋርም ይጋጫል ። ደግሞም በመስቀል ላይ በንስሃ የተመለሰውም ወንበዴ አልዳነም ማለት ነው ። ድፏል ብለን የምናስብ ከሆነ ሆነ ደግሞ ያለ ጥምቀት ወደ እግዚአብሔርን መንግስት መግባት ይቻላል ማለት ነው ያለ ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ከተቻለ ደግሞ ያለጥምቅ ወደእግዚአብሔር መንግስ መግባት አይቻልም ማለት ስህተት ነው ።

፪ኛ, የዮሐንስን ጥምቀት ነው ። ምክንያቱም የዮሐንስ ጥምቀት ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መምጫ መሰረታዊ ነገር ነው ። ስለዚህ ኢየሱስ ኒቆዲሞስን እያለ ያለው ሂድና ዮሐንስ ጋር ተጠመቅ እያለ ነው ። ይህ ምልከታ ደግሞ ስህተት ሊሆን የሚችለው የኢየሱስ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ የዮሐንስ አገልግሎት አብቅቷል ። ይህ ከሆነ ደግሞ ኢየሱስ እንዴት ወደ ዮሐንስ ጋር ሄደህ ተጠመቅ ሊለው ይችላል ?

፫ኛ, ውሃ የሚለው ቃሉን ለማመልከት ነው የሚሉ አሉ ። ይህንን እንዲሉ ያስቻላሉ የእግዚአብሔር ቃል በውሃ ከማንፃት ጋር ተያይዞ ስለቀረበ ነው ። ለምሳሌ ፦ ኤፌሶን ፭፥፳፮ (አዲሱ መ.ት) ። “በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፣” ይህ ክፍል እና ሌሎችንም ክፍሎች እንደ ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውሃ ማለት ቃሉ ነው የሚለውን ትርጉም የሚሰጡ አይደሉም ።

የተሻለው አተረጓገም ብዬ የማስበው በእዚህ ክፍል ውሃ የመንፈስን ቅዱስ ምልክት ሆኖ ነው የቀረበው ።

ለምሳሌ ውሃ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተያይዞ እንደቀረበ መመልከት እንችላለን ። ኢሳይያስ 44 (አዲሱ መ.ት) ። 3 በተጠማ ምድር ላይ ውሃ፤ በደረቅ መሬት ላይ ወንዞችን አፈሳለሁና፤ መንፈሴን በዘርህ፣ በረከቴንም በልጅ ልጅህ ላይ አወርዳለሁ። 4 እነርሱም በለመለመ መስክ ላይ እንደ ሣር፣ በወንዝ ዳር እንደ አኻያ ዛፍ ይበቅላሉ።

– ኤርምያስ 2፥13 (አዲሱ መ.ት) ። ““ሕዝቤ ሁለት ኀጢአት ፈጽመዋል፣ ሕያው የውሃ ምንጭ የሆንሁትን፣ እኔን ትተዋል፤ ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች፣ ለራሳቸው ቈፍረዋል።”

– ሕዝቅኤል 47 (አዲሱ መ.ት) ። 1 ከዚያም ያ ሰው ወደ ቤተ መቅደሱ መግቢያ መልሶ አመጣኝ፤ ከቤተ መቅደሱ መድረክ ሥር ውሃ እየወጣ፣ ወደ ምሥራቅ ይፈስ ነበር፤ ቤተ መቅደሱ ለምሥራቅ ትይዩ ነበርና። ውሃው ከቤተ መቅደሱ በስተ ደቡብ በኩል፣ በመሠዊያው ደቡብ በኩል፣ ሥር ሥሩን ይወርዳል። 2 ከዚያም በሰሜኑ በር በማውጣት በውጭ አዞሮ በምሥራቅ አቅጣጫ ወዳለው የውጭ በር መራኝ፤ ውሃውም በደቡብ በኩል ይፈስ ነበር። 3 ያም ሰው የመለኪያውን ገመድ በእጁ ይዞ ወደ ምሥራቅ በመሄድ፣ አንድ ሺህ ክንድ ለካ፤ ከዚያም እስከ ቍርጭምጭሚት በሚደርሰው ውሃ ውስጥ መራኝ፤ 4 ቀጥሎም አንድ ሺህ ክንድ ለካ፤ እስከ ጕልበት ወደሚደርስም ውሃ መራኝ፤ ከዚያም ሌላ አንድ ሺህ ክንድ ለካ፤ እስከ ወገብ ወደሚደርስም ውሃ መራኝ። 5 እንደ ገናም አንድ ሺህ ክንድ ለካ፤ አሁን ግን ልሻገረው የማልችል ወንዝ ሆነ፤ ምክንያቱም ውሃው ስለ ሞላና ጥልቅ ስለ ነበረ፣ በዋና ካልሆነ በስተቀር በእግር ሊሻገሩት የማይቻል ነበረ።

– ዘካርያስ 14፥8 (አዲሱ መ.ት) ። “በዚያን ቀን የሕይወት ውሃ ከኢየሩሳሌም ይፈልቃል፤ እኩሌታው ወደ ምሥራቁ ባሕር፣ እኩሌታውም ወደ ምዕራቡ ባሕር ይፈሳል፤ ይህም በበጋና በክረምት ይሆናል።”

– ዮሐንስ 4፥10 (አዲሱ መ.ት) ። “ኢየሱስም፣ “የእግዚአብሔርን ስጦታ ብታውቂና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑን ብትረጂ ኖሮ፣ አንቺው በጠየቅሽው፣ እርሱም የሕይወትን ውሃ በሰጠሽ ነበር” ሲል መለሰላት።”

ስለዚህ ከውሃ መወለድ ማለት ከመንፈስ መወለድ ነው ። እዚህ ጋር አንድ ጥያቄ ያስነሳል ። ከውሃ የሚለው ከመንፈስ የሚለውን ትርጉም ከያዝን ከመንፈስ እና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም የሚልን ትርጉም ይሰጠናል ። ነገርግን የግሪኩን ቃል በክፍሉ አውድ በትክክል ከተረጎምን ይህንን አይሰጠንም ። ምክንያቱም እና የሚለው አያያዥ ቃል ሁለት የተለያዩ ነገሮችን የሚያመለክት ስለሆነ ። ነገርግን እና የምትለው ቃል ግሪክ ላይ Καὶ የምትል ቃል ስትሆን ማለትም ተብላ መተርጎም ትችላለች ። ይህ ከሆነ ከጥሎ ያለው የመጀመሪያውን የሚያብራራ ነው ። ማለትም ወሃ የሚለው መንፈስ በሚለው የተብራራ ነው ። ስለዚህ ኢየሱስ እያለ ያለው እንደዚህ ነው ፦ ሰው ከውሃ ማለትም ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም ነው ።

ስለሁለት የተለያየ ነገር እያወራ እንዳልሆነ የምንረዳው ወይንም ስለአንድ ነገር እያወራ እንደሆነ የምንረዳው ቀጥሎ ባሉ ቁጥሮች ውሃን አይጠቀመም ነገርግን መንፈስ የሚለውን ብቻ ይዞ ይቀጥላል ። ለምሳሌ ፦ ዮሐንስ 3 (አዲሱ መ.ት) ። 5 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤ 6 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው። 7 ‘ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ’ ስላልሁህ አትገረም፤ 8 ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው።”

ሌላኛው ከዳግመኛ መወለድ ጋር ተየይዞ የሚያቀርቡት የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባብ ቲቶ 3:5 ላይ ያለው ነው ። –

ቲቶ 3፥5 (አዲሱ መ.ት) ። “ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤” ይህ ክፍል በመሰረቱ ዳግም ልደት በውሃ ጥምቀት ይገኛል ለሚለው እንደ ማስረጃ ማቅረብ ተገቢ ነው ብዬ አላስብም ። ምክንያቱም ጥምቀት የሚል ቃል እራሱ አይጠቀምም ። ስለዚህ ስለጥምቀት ካላወራ ይህንን ክፍል ከጥምቀት ጋር እያያይዞ መተርጎም ስህተት ነው ።

**– ማርቆስ 16፥16 (አዲሱ መ.ት) ። “ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።”**

ኦርቶዶክሶች እና ካቶሊኮች ያመነ የተጠመቀ ይድናል የሚለውን ጥቅስ እንቀበላለን ይላሉ እንጂ አይቀበሉትም ። ምክንያቱም የህፃናት ጥምቀት ለድነት ነው ብለው ስለሚያምኑ ። ህፃናት ደግሞ አምነው አይደለም የሚጠመቁት ስለዚህ ያመነ የተጠመቀ የሚለውን ክፍል የሚቀበሉት Protestantኡን ለመቃወም እንጂ የሚያምኑበት ጥቅስ አይደለም ። ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ ይህንን ክፍል እንዴት እንመለከተዋለን ? ይህንን ክፍል በተመለከተ ውስጣዊ እና ውጫዊ መረጃዎችን ለመመልከት እንሞክራለን ።

– ውጫዊ መረጃዎች

Clement of Alexandria (c. 150-215 AD), Origen (c. 185-253 AD) ኦሪገን ፣ Jerome (c. 347-420 AD) (ጀሮምና), Eusebius (c. 260-340 AD) (ዩሲቢየስ) ከቁጥር 9-20 ያለውን የለም ይላሉ ወይንም የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል አካል አይደለም ይላሉ ። ይህ ብቻ ሳይሆን Codex Sinaiticus (ኮዴክስ ሳይናቲክስ) እና Codex Vaticanus (ኮዴክስ ቫቲካነስ) ቀደምት manuscripts ከቁጥር 9-20 ያለውን አያካትቱም ። Codex Sinaiticus እና Codex Vaticanus ከጥንታዊ ቅጂዎች መካከል ሁለቱ ቀደምት ሲሆኑ በእድሜያቸው ፣ በጥራታቸው እና በጥንታዊ የክርስትና ጽሑፋዊ ወጎች ላይ በሚሰጣቸው ልዩ ቦታ ምክንያት ታማኝ የመረጃ ምንጭ ተደርገው ይወሰዳሉ ።

– የውስጥ ማስረጃዎች

1ኛ, ትንሳኤውን በተመለከተ የተሰጠው ዝርዝ ፦ በማቴዎስ፣ በሉቃስ እና በዮሐንስ ውስጥ እንዳሉት ዝርዝር የትንሳኤ መገለጦች የማርቆስ የተለየና ድንገተኛ ሆኖ ስለሚታሰብ ከ9-20 ያሉ ቁጥሮች በኋላ የተጨመረ ነው ወደሚለው መደምደሚያ አንዳንዶችን አድርሷል ።

2ኛ, ምልክቶች እና ተአምራት ፦ እባቦችን መያዝ እና መርዝ መጠጣትን መካተታቸው እንደ ችግር ሆኖ ታይቷል ። ምክንያቱም እነዚህ አገላለፆች በቀሪው የአዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ ስላልታዩ እና የጥንቶቹ ክርስትያኖች ልምምድ አካል ስላልነበሩ ። አንዳንዶች እነዚህን ጥቅሶች ይበልጥ ማራኪ ወይም ተአምራዊ ትኩረት ያለው በኋላ ላይ እንደጨመሩ ይቆጥራሉ።

3ኛ, የቃላት አጠቃቀሙ ፦ በዚህ ክፍል ውስጥ 18 ቃላቶች በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሌላ ቦታ ተጠቅሞት አያውቅም ። ከቁጥር 9-20 ያሉት ከ 70 በመቶ በላይ ከተቀሩት የማርቆስ ክፍል ውስጥ የሉም ። የቃላት አመራረጡ ብቻ ሳይሆን የአረፍተ ነገር አቀማመጡም ከተቀሩት የማርቆስ ክፍሎች የተለዩ ናቸው ።

– 1ኛ ጴጥሮስ 3፥21 (አዲሱ መ.ት) ። “ይህም ውሃ አሁን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል፤ ይህም የሰውነትን እድፍ በማስወገድ ሳይሆን በንጹሕ ኅሊና በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ መማፀኛ ነው፤

የሚያድናችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው፤”

– አስቀድም ምን እያለ አይደለም የሚለውን እንመልከት ።

የውሃ ጥምቀት ያድናችኋል እያለ አይደለም ።

ይህንን ለመረዳት አስቀድመን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ **ያድናችኋል** ሲል እነዚህ የጴጥሮስ መልዕክት ተደራሲያን ይህ ደብዳቤ እስኪፃፍ ድረስ አልዳኑም ማለት ነው ? ሁለተኛ የውሃ ጥምቀት ነው ብለን ብናስብ አማኞች ከሆኑበት ይህ ደብዳቤ እስኪፃፍ ድረስ አልተጠመቁም ማለት ነው ?

ሌላኛው ያድናችኋል ሲባል ከምን ብሎ መጠየቅ መሰረታዊ ነገር ይመስለኛል ። ምክንያቱም መዳን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዘላለም ህይወት ጋር ብቻ የተያያዘ ስላልሆነ ። ለምሳሌ ፦ – 1ኛ ጢሞቴዎስ ፪፥15 (አዲሱ መ.ት) ። “ይሁን እንጂ ሴት በእምነትና በፍቅር፣ በቅድስናም ራሷን እየገዛች ብትጸና ልጅ በመውለድ <u>ትድናለች</u>።” ስለዚህ ወላድ ሁሉ የዘለአለም ህይወት ያገኛል ማለት ነው ? በፍፁም ። ስለዚህ መዳን ሲባል ሁል ጊዜ እንድ አይነት ትርጉም አይኖረውም ። ስለዚህ የጴጥሮስ መልዕክት ተደራሲያ ይህ መልዕክት ከመፃፉ አስቀድሞ አማኞች ከሆኑ ወይንም የዳኑ ከሆኑ አሁን **ያድናችኋል** ሲሊ ከሌላ ነገር መሆን አለበት ።

– አሁን ያድናችኋል ሲል ምን እያለ ነው ?

ይህንን *Explicitly* እንደዚህ ነው ማለት ከባድ ነው ። ነገር ግን ምን አይደለም የሚለውን በእርግጠኝነት የውሃ ጥምቀት አይደለም ማለት እችላለሁ ። ምን እያለ እንደሆነ ግን እንዲህ እያለ ነው ማለት ባልችልም የተወሰነ አቅጣጫ የሚሰጡ ነገሮችን መመልከት እንችላለን ።

1ኛ, ይህም ውሃ እያለ ያለው የኖህን ዘመን የጥፋት ውሃ እንጂ ጥምቀትን አይደለም ። ነገር ግን የኖህ ዘመን ውሃ የጥምቀት ምሳሌ ነው ። የየትኛውም ጥምቀት እንደሆነ አልገለፀልንም ። ስለዚህ የኖህ ዘመን ውሃ ሲል ዘለን የውሃ ጥምቀት ወደሚለው መሄድ የለብንም ። ምክንያቱም የኖህ ዘመን ውሃ የጥፋት መሳሌ ነው ፣ ጥምቀት ደግሞ የጥፋት ምሳሌ ሳይሆን የመዳናችን ውጫዊ ገፅታ ነው ። ስለዚህ ሊሆን የሚችለው የመከራን ጥምቀት ነው ። በመከራ ጥምቀት ጥምቀት አልፋችሁ አሁን ካጋጠማችሁ መከራ ትድናላችሁ እያለ ሊሆን ይችላል ።

በመሰረቱ ኖህና ቤተሰቡ የዳኑት በውሃው ሳይሆን በሰሩት መርከቡ ነው ። የሰሩት መርከብ ደግሞ በእምነት ነው ። – ዕብራውያን 11፥7 (አዲሱ መ.ት)። “ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት ሠራ፤ በእምነቱ ዓለምን ኰነነ፤ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።” ስለዚህ ኖህ የዳነው በእምነቱ ነው ማለት እንችላለን ።

እስካሁን በተመለከትናቸው የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጥምቀት ለድነት አሰንዳልሆነ ግልጽ ነው ። ከእዚህ በተጨማሪ ደግሞ ያለ ጥምቀት ድነት እንደሚገኝ የሚያሳዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባትን እንመልከት ። ለምሳሌ ከኢየሱስ ጎን የተሰቀለው ሳይጠመቅ ነው የዳኑት ። ይህንን ስንል የማይዋጥላቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ***Exceptional*** ነው ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ የውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ ነው በትዕዛዝ መልክ የተቀመጠው ይላሉ ። *Exceptional* ሆኖም ሰዎች ከዳኑ ያለ ጥምቀት መዳናችን ያመለክታል ደግሞም ከትዕዛዙ አስቀድሞ ሰዎች ከዳኑ ያለ ጥምቀት ድነዋል ። ዋናው ሰው ያለጥምቀት መዳን ይችላል የሚለውን ሙግት ማሳየት ነው አላማው ።

ደግሞ ሐዋሪያት ስራ 10 ላይ ያለው የቆርኖሊዎስ ታሪክ እንደ ማስረጃ ሆኖ መቅረብ ይችላል ። የቆርኖሌዎስን ታሪክ ከዘረዘረ በኋላ ፦ ሐዋርያት 10 (አዲሱ መ.ት) ። [47] “እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ፣ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?” [48] ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ፣ ጴጥሮስ ጥቂት ቀን ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ለመኑት።

መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ከጥምቀት በፊት ነው ። ከጥምቀት በፊት መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው የመዳናቸው ምልክት እና ማረጋገጫ ነው ። ለምሳሌ ፦ – ሮሜ 8፥9 (አዲሱ መ.ት) ። “እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም።”

– ኤፌሶን 1፥13 (አዲሱ መ.ት) ። “እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም፣ በእርሱ በመሆን ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል።” ስለዚህ በእዚህዉ ምንባብ ተመስርተን ሰዎች ያለ ጥምቀት ይድናሉ ማለት እንችላለን ። መፅሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ስንመለከት መዳን በእምነት ብቻ ፣ በፀጋ ብቻ እና በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ይገልፅልናል ። – ኤፌሶን 2 (አዲሱ መ.ት) ። [8] በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ [9] ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤ስለዚህ ሰዎች በእምነት ብቻ ይድናሉ እንጂ ሌሎች ኃይማኖታዊ ስርአቶችን እና ስራዎችን ከእምነት ጋር በመጨመር አይድኑም ።

ከእዚህ በመቀጠል በዋናነት ማን ይጠመቅ ? (*Subjects of Baptism*) ፣ እንዴት እንጠመቅ ? (*Mode of Baptism*) ፣ በማን ስም እንጠመቅ? የሚሉትን እንመለከታለን ። ከእዚያ አስቀድሞ ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው ብለው መከራከሪያ ከመያቀርቡት መካከል ሌላ የሚያነሱትን ሁለት ምንባብ አንስቼ መልስ ለመስጠት ልሞክርና ወደ ርዕሰ ጉዳያችን እናልፋለን ። ሮሜ 6:3-6 እና ገላትያ ለ3:27 ላይ በመመስረት ከክርስቶስ ጋር የምንሞተው እና የምንነሳው በውሃ ጥምቀት ነው የሚሉ አካላትም ቤተ እምነቶችም አሉ ። ሰው ከክርስቶስ ጋር ካልሞትን ደግሞም ካልተነሳን ደግሞ አልዳነም ማለት ነው ይላሉ ። ስለዚህ ለእነርሱ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ ።

በጣም ብዙ ሰዎች ኤፌሶን 4 ላይ በመመስረት ጥምቀት አንድ ነው ወይንም አንዲት ጥምቀት ብቻ አለ ይላሉ ። – ኤፌሶን 4፥5 (አዲሱ መ.ት) ። “አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤” ይህ ግን መፅሐፍ ቅዱስን በትክክል ካለማጥናት የመነጨ ድምዳሜ ነው ። ኤፌሶን ላይ አንዲት ጥምቀት ሲል ጥምቀት አንድ ብቻ ነው የሚለውን በአዕምሮአችን እንድናስብ አይደለም ።

ነገር ግን ጥምቀትን ከአንድ በላይ አድርጎ *Plural* አድርጎ መፅሐፍ ቅዱስ ይገልፅልናል ። – ዕብራውያን 6 (አዲሱ መ.ት) ። [1] ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል፤ [2] እንዲሁም ስለ ጥምቀቶች፣ እጆችን ስለ መጫን፣ ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ ትምህርት እንደ ገና አንመሥርት። ስለ ጥምቀቶች በማለቱ ጥምቀትን *plural* አድርጎ ገልፆታል ። በእኔ ዝግጅት 5 የጥምቀት አይነቶችን አስቀምጣለሁ ። አንዳንዶች እስከ ሰባት ያስቀምጣሉ ። እኔን የሚያሳምነኝ ግን አምስቱ ብቻ ናቸው ።

*1, Baptism of Repentance* የንስሐ ጥምቀት ። ይህ ከመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ጋር የተያያዘ ነው ። የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የኢየሱስን መምጣት መንገድ በማዘጋጀት የንስሐ ጥሪ ነበር። ይህ ጥምቀት ከክርስቲያናዊ ጥምቀት የተለየ ነበር ።

2, Water Baptism (Christian Baptism) የውሃ ጥምቀት (የክርስቲያን ጥምቀት) ። ይህ በኢየሱስ ጥምቀት ለደቀመዛሙርቱ በተሰጠው ትእዛዝ ውስጥ የተካተተው ነው ። ማቴዎስ 28: 19 ። አላማውን በተመለከተ በኋላ ላይ በስፋት የማቀርብ ቢሆንም በአጭሩ ለመግለጽ ያህል የውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር እንደሞትን እና እንደተነሳን ማሳያ እንዲሁም ከኃጢአት እንደታጠብን በምሳሌነት የምናደርገው ስርአት ነው ። የውሃ ጥምቀት አላማ ። ከአማኞች ጋር መተባበርን ለመግለጽ ነው ። “እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ።” — 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥2 (አዲሱ መ.ት) ።

3, Baptism of Fire (የእሳት ጥምቀት) ። ይህ ፍርድን ወይም መንጻትን የሚያካትት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው ። ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ በማቴዎስ 3፡11 ላይ ተናግሯል ። ይህም ከፍርድ ጋር የተያያዘ ነው ። – ማቴዎስ 3 (አዲሱ መ.ት) 10 እነሆ፤ ምሣር የዛፎችን ሥር ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል። 11 “እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣ ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ ይመጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። 12 መንሹ በእጁ ነው፤ ዐውድማውን ያጠራል፤ ስንዴውን በጐተራ ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።”

4, Baptism of Suffering የመከራ ጥምቀት ። ይህ ዓይነቱ ጥምቀት የሚያመለክተው ኢየሱስ የሚቀበለውን መከራ በተለይም ስቅለቱን ነው ። ይህ በማርቆስ 10፡38–39 ውስጥ ተገልጿል ። ማርቆስ 10 (አዲሱ መ.ት) 38 ኢየሱስም፣ “የምትለምኑትን አታውቁም፤ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?” አላቸው። 39 እነርሱም፣ “አዎን እንችላለን” አሉት። ኢየሱስም፣ “እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ፤ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤ ። በእዚህ ክፍል ኢየሱስ የሚገጥሙትን ፈተናዎችና መከራዎች በማሳየት ስለ ራሱ ስለ መከራ “ጥምቀት” ሲናገር እናስታውሳለን ። የመከራ ጥምቀት አላማ አማኞችን ብቁ አድርግ ማሳለፍ ነው ።

5, Baptism of the Holy Spirit (የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት) ። ይህ ጥምቀት አላማው ለአንድነት የሚደረግ ጥምቀት ነው ። በሁለት አቅጣጫ :- አንደኛው ከራሱ ከክርስቶስ ጋር ሲሆን 2ኛ, ከቅዱሳን ጋር ወይንም የክርስቶስ አካል ከሆነችው ቤተክርስቲያን ጋር ነው ። — 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 (አዲሱ መ.ት) ። “አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል።”

– ሐዋርያት 11 (አዲሱ መ.ት) ። 15 “እኔም ገና መናገር ስጀምር፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ። 16 በዚህ ጊዜ፣ ‘ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ’ ሲል ጌታ የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ። 17 እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ለእነርሱም ከሰጣቸው፣ ታዲያ፣ እግዚአብሔርን መቋቋም እችል ዘንድ እኔ ማን ነኝ?” 18 ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ “ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቷቸዋል ማለት ነዋ።”

በእዚህ መንገድ የጥምቀቶችን አላማ ከተረዳን የሮሜን እና የገላትያ አውድ ከአራቱ የጥምቀት አይነቶች የሚቀርቡ ለይትኛው ነው ? የሚለውን እንጠይቃለን ። ስለ አንድነት ነው የሚያወራው ። ስለአንድነት እያወራ ከሆነ አንድ ስለሚያደርገው ጥምቀት እያወራ መሆን መቻል አለበት ። እርሱም የመንፈስ ጥምቀት ነው።

– ሮሜ 6 (አዲሱ መ.ት) ። 3 ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4 ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣ እኛም እንዲሁ በአዲስ

ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል። ⁵ በሞቱ ከእርሱ ጋር እንደዚህ ከተባበርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በርግጥ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን። ⁶ ከእንግዲህ የኀጢአት ባሮች እንዳንሆን፣ የኀጢአት ሰውነት እንዲሻር አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤

ይህ የሮሜ መፅሐፍ እየነገረን ያለው የምንጠመቅበት አላማ አንድ እንድንሆን ዘንድ ነው ይለናል ። ስለዚህ በቀላል መንገድ ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አላማው አንድ የሚያደርገው ጥምቀት የቱ ነው ብለን ማመሳከር ብቻ ነው የሚጠበቅብን ። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው ። የውሃ ጥምቀት አይደለም ። የውሃ ጥምቀት አንድ ለመሆን የሚደረግ ጥምቀት ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆነ ሰው አንድ መሆኑን ማሳያ ነው ።

– ገላትያ ፫፥፳፯ (አዲሱ መ.ት) ። “ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና።” ይህም ከሮሜው ጋር ተመሳሳይ ነው ። ምክንያቱም የተጠመቃችሁት አንድ እንድትሆኑ ነው ይላል ። ስለዚህ አንድ የሚያደርገው ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው ።

## <u>ማን ይጠመቅ ? (Subjects of Baptism)</u>

እዚህ ላይ በዋናነት ሁለት ምልከታዎች አሉ ። እነርሱም *Pedo-baptism* እና *credo-baptism* ናቸው ። *Pedo-baptism* ህፃናት መጠመቅ አለባቸው የሚል ሲሆን ፣ *credo-baptism* ደግሞ ከእምነት በኋላ የሚደረግ ጥምቀት ወይንም አንድ ሰው ኃይማኖታዊ እውቀት ካለው በኋላ የሚያደረገው ተግባር ነው ብሎ ማመን ነው ።

*pedo baptism*ን የሚያምኑ አብያተክርስቲያናት ለምሳሌ ፦ *Lutheran, Presbyterian, Anglican/Episcopal Church* እና *Methodist*ኦች ናቸው ። ከእነዚህ መካከል በዋነናነት የሁለቱን እንመልከት (የ *Presbyterian* እና የ *Lutheran* ) ሁለቱም የህፃናት ጥምቀትን ቢያምኑም በመካከላቸው የተወሰነ ልዩነት አለ ።

**– *Presbyterian***

የአማኝ ቤተሰብ መጠመቅ አለባቸው የሚለውን ሉዊስ በርኮፍ የሚያቀርበው መከራከሪያ ግልፅ ስለሆነ ያንን ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

፩ኛ, በአሮጌው ኪዳን ህፃናት ይገረዙ ነበር ። ስምንት ቀን የሞላው ማንኛውም እስራኤላዊ ይገረዝ ነበር ። – ዘፍጥረት ፲፯ (አዲሱ መ.ት) ። ¹⁰ አንተና ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠብቁት ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። ¹¹ ስለዚህ ሁላችሁም ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል ላለው ኪዳን ምልክት ይሆናል። ¹² የሚመጣውም ትውልድ ሁሉ፣ ማንኛውም ወንድ ልጅ፣ ስምንት ቀን ሲሞላው ይገረዝ፤ እንደዚሁም በቤትህ የተወለደውና ከውጭ በገንዘብ የተገዛ ባዕድ ሁሉ ይገረዝ። ¹³ በቤትህ የተወለደም ሆነ በገንዘብህ የተገዛ ሁሉ መገረዝ አለበት፤ በሥጋችሁ የሚፈጸመው ይህ ኪዳኔ የዘላለም ኪዳን ይሆናል።

፪ኛ, ግርዘት እና ጥምቀት የሚዛመዱ ናቸው ። በግርዘት እና በጥምቀት መካከል ያለውን ተዛምዶ ቆላሲስ ላይ እናገኛለን ። – ቆላስይስ ፪ (አዲሱ መ.ት) ። ¹¹ በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤

በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ፤ [12] በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፣ እርሱን ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር ኀይል በማመን ከእርሱ ጋር ደግሞ ተነሣችሁ። በእዚህ ክፍል የግርዘትን እና የዝምቀትን ግኑኝነት በግልጽ እንመለከታለን ይላል ።

3ኛ, የአማኞች ቤተሰብ ጥምቀትን መፅሐፍ ቅዱስ ይናገራል ይላል ። የልድያ ቤተሰብ (ሐዋ 16:15) ፣ የወህኒ ቤቱ ጠባቂ ቤተሰብ (ሐዋ 16:33) ፣ እና የእስጢፋኖስን ቤተሰዎች መጠመቅ ( 1ኛ,ቆሮ 1:16) ። እነዚህ ክፍሎች የህፃናትን ጥምቀት ይደግፋል ብሎ ያስባል ።

በእነዚህ ሶስቱ ሀሳብ ላይ ሙግት ላቅርብ ።

1ኛ, ጥምቀት እና ግርዘት በብዙ መንገድ የሚመሳሰል ቢሆንም በሁሉም መንገድ ግን የሚመሳሰሉ አይደሉም ። በተለይም በሚያስተላልፉት ምሳሌነት ላይ ልዩነት አላቸው ።

2ኛ, የህፃናትን ጥምቀት ለመደገፍ የቀረቡት የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት አሳማኝ አይደሉም ። ደግሞም ግምት ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ነው ። ደግሞም የጠቀሱት ክፍል እራሱ መልሶ እነርሱን የሚቃወም ነው ። ለምሳሌ :- – ሐዋርያት 16 (አዲሱ መ.ት) ። [31] እነርሱም፣ “በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ” አሉት። [32] <u>ከዚያም ለእርሱና በቤቱ ላሉት ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ተናገሩ።</u> [33] የወህኒ ቤት ጠባቂውም ሌሊት በዚያኑ ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፤ ወዲያውም እርሱና ቤተ ሰቡ ሁሉ ተጠመቁ። በእዚህ ክፍል ለእርሱና በቤተሰቡ ላሉ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ከተናገሩ ፤ ቃሉ የተነገራቸው ሰዎች ቃሉን መረዳት እና ማመን የሚችሉ ሰዎች መሆን መቻል አለባቸው ።

– የእስጢፋኖስ ቤተሰዎች ደግሞ ትልልቅ ሰዎች እንደነበሩ በእዚሁ በቆሮንቶስ መፅሐፍ መመልከት እንችላለን ። – 1ኛ ቆሮንቶስ 16፥15 (አዲሱ መ.ት) ። “የእስጢፋኖስ ቤተ ሰዎች በአካይያ የመጀመሪያዎቹ አማኞች እንደሆኑና ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደ ሰጡ ታውቃላችሁ። ወንድሞች ሆይ፤ ይህን እለምናችኋለሁ፤”

በጠቅላላ የ Presbyterian ሀሳብ እንደሚከተለው ነው ።

1ኛ, ሰው በውሃ ጥምቀት ቅጽበት ዳግም ላይወለድ ይችላል ። ይህ ማለት ግን ጥምቀት አያድንም ማለት አይደለም ይላሉ ።

2ኛ, ሰዎች በውሃ ተጠምቀው መንፈስ ቅዱስን ላይቀበሉ ይችላሉ ወይንም ዳግም ላይወለዱ ይችላሉ ። ለእዚህም ደግሞ ሰማሪያዊው ሰው ጠንቋዩ ስምኦን ምስክር ነው ። ሐዋ 8:13-25 ።

– ሐዋርያት 8 (አዲሱ መ.ት) ። [13] ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር አምኖ ተጠመቀ፤ ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደረገውን ምልክትና ታላቅ ታምራት አይቶም ተገረመ። ... [18] ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ፣ ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላቸው፤ [19] “እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ለእኔም ስጡኝ።” [20] ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፤ “የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃልና፣ አንተም ገንዘብህም አብራችሁ ጥፉ! [21] ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ፣ አንተ በዚህ አገልግሎት ድርሻ ወይም ዕድል ፈንታ የለህም። [22] አሁንም ስለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ፤ ወደ ጌታም ጸልይ፤ ምናልባት ይህን የልብህን ሐሳብ ይቅር ይልህ ይሆናል፤ [23] ምክንያቱም በመራራነት ተሞልተህ፣ በዐመፅ ሰንሰለት ተይዘህ አይሃለሁና።” [24] ሲሞንም መልሶ፣ “ከተናገራችሁት ምንም ነገር እንዳይደርስብኝ ጌታን ለምኑልኝ” አላቸው።

3ኛ, እንደ ሰማሪያ ሰዎች በውሃ ከተጠመቁ በኋላ ዘግይተው መንፈስ ቅዱስን ሊቀበሉ ይችላሉ ። ሐዋ 8:13–25።

– ሐዋርያት 8 (አዲሱ መ.ት) ። [15] እነርሱም ሰማርያ በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤ [16] ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ ገና መንፈስ ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር። [17] ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።

ለእዚህም ነው ከእዚህ በፊት Absolute necessityን አይቀበሉም ያልኩት ። እንደዚህ የሚቀበሉት ካቶሊኮች ናቸው ። ያለ ጥምቀት ሰው በጭራሽ አይድንም ፣ የኃጢአት ይቅርታን አያገኝም ፣ ደግም ውልደትን አያገኝም ይላሉ ። ይህ በ ፕሮቴስታንቱ አለም ተቀባይነት የለውም ። Lutheran እና Presbyterian ordinary necessity ነው የሚቀበሉት ። ድነትን እንቀበልበታለን ፣ ዳግሞ ልደትን እንቀበልበታለን ፣ የኃጢአት ይቅርታን እንቀበልበታለን ። ነገርግን በምንም መንገድ ከእዚህ ውጪ አይገኝም ማለት አይደለም ይላሉ ። ምክንያቱም ሰው ሳይጠመቅ ድኖ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለ ይላሉ ። በቀላሉ ነገሩን ለመረዳት ሰው በእምነት ብቻ ያለ ጥምቀት እና የጌታ እራት ይድናል ። ስለዚህ Absolute necessity Faith ነው ለ Lutheran እና ለ Presbyterian ። ሰው ያለ እምነት አይድንም ። ያለ ቅዱሳት ሚስጥራት ግን ይድናል ብለው ያምናሉ ።

– Lutheran

ለሉተራውያን ጥምቀት ምልክት ብቻ ሳይሆን ሕፃኑን ለማዳን እና የኃጢአት ይቅርታን ለማስገኘት እግዚአብሔር የሚሠራበት ዘዴም ነው ። ህፃኑ ህፃን በሆነበት ሁኔታ ቢያምንም ነገርግን እምነቱን መግለጽ አይችልም ።

እምነት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ እንጂ የሰው የማስተዋል ብቃት ውጤት አይደለም ። – ኤፌሶን 2፥8 (አዲሱ መ.ት) ። "በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤" ስለዚህ ሰው በዕድሜው ብዛት እና በማስተዋሉ የዳነ አይደለም ማለት ነው ።

ከእዚህ በመነሳት ህፃናት ማመን ስለማይችሉ አናጠምቃቸውም ማለት እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠውዉ ስጦታ እነርሱ ህፃን ስለሆኑ ብቻ ነፍጓቸዋል ማለት ነው ? ብለው ይጠይቃሉ ። እኛ ያመንነው እንዴት ነው ? ፣ አሳቢዎች ስለሆንና ማገናዘብ ስለምንችል ነው ብለው ይጠይቃሉ ። ወይስ እግዚአብሔር በበጎ ፈቃዱ የሚያድንን እምነት በነፃ ስለሰጠን ነው ?

እግዚአብሔር በእኛ ሞኝነት ሳይከደብ ለእኛ እምነትን በውስጣችን ካኖረ በህፃናት ህፃንነት ሳይገደብ እንዴት በህፃናት ውስጥ እምነትን አይፈጥርም? ይላሉ ። ስለዚህ እግዚአብሔር በህፃናት ውስጥ እምነትን ይፈጥራል ይላሉ ። ለእዚህም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ለማቅረብ ይሞክራሉ – መዝሙር 22፥9 ። "አንተ ግን ከሆድ አውጥተኸኛልና፥ በእናቴ ጡት ሳለሁም በአንተ ታመንሁ።" በእዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ጡት የሚጠቡት ህፃናት ሳይቀሩ እንኳን በእግዚአብሔር እንደሚታመኑ ነው ።

– credo-baptism

የ credo baptismን አስተሳሰብ ከሚዙ ቤተ እምነቶች መካከል ፦ ባፕቲስቶች/Baptist ወይንም (የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተክርስቲያን) ፣ ሜኖናይቶች(Mennonite ) ወይንም አናባፕቲስት (Anabaptists) (መሰረተ ክርስቶስ) እና Pentecostal and Charismatic Churches ወይንም (ሙሉ ወንጌል) ናቸው ።

የ ሜኖናይቶች(*Mennonite* ) መስራች ሜኖን ሲሞንስ ህፃናት መጠመቅ አለባቸው እና በውሃ ጥምቀት ይድናሉ ብሎ ማለት ከንቱ የሰዎች እምነት ነው ብሎ ቢያምንም ነገርግን ህፃናት ያለ ውሃ ጥምቀት እንደሚድኑ እግዚአብሔር ቃል ገብቷል ብሎም ያምናል ። ስለዚህ ህፃናት ማመን ባይችሉም ፣ ባይጠመቁም ይድናሉ ብሎ ያምናል ።

– የባፕቲስት

ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ብቻ የተሰጠ ስርአት ነው ብለው ያምናሉ ። ጥምቀት በፍፁም ልብ ማመንን (ሐዋ ፰:፴፯) ፣ ንስሃ መግባትን (ሐዋ ፪:፴፰) የሚከተል ተግባር እንጂ በህፃንነታችን ማመን ይቅርና ቤተሰቦቻችንን እንኳን ማወቅ በማንችልበት ጊዜና ሁኔታ ያለእኛ እምነት ቤተሰቦቻችን ውሳኔ የሚደረግ ስርአት አይደለም ። የህፃናት ጥምቀት ጊዜን እና ውሃን ከማባከን ባለፈ ምንም ፋይዳ የለውም ። እግዚአብሔር ባላዘዘው ነገር ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አሰራር ሆነ ጣልቃ ገብነት ስለማይኖር የህፃናትን ጥምቀት እንደ ጥምቀት አንቆጥረውም ይላሉ ።

– ሐዋርያት ፪፥41 (አዲሱ መ.ት) ። “ቃሉን የተቀበሉትም ተጠመቁ፤ በዚያ ቀን ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች በቍጥራቸው ላይ ተጨመሩ።”

– ሐዋርያት ፰፥1፪ (አዲሱ መ.ት) ። “ነገር ግን ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው በመቀበላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤”

– ሐዋርያት ፰፥፴፯ (አዲሱ መ.ት) ። “ፊልጶስም፣ “በፍጹም ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትችላለህ” አለው። ጃንደረባውም፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ” ሲል መለሰለት፤”

ይህ ክፍል ቆንጆ ማሳያቢሆንም ነገር ግን እዚህ ላይ ክርክር አለ ። አንዳን የጥንት *manuscripts* ፰:፴፯ን አያካትቱም ። ለምሳሌ :- *Codex Sinaiticus and Codex Vaticanus* አያካትቱትም ። አንዳንድ *Translations* ቁጥር ፴፯ን አያካትትም ።

– ሐዋርያት 10 (አዲሱ መ.ት) ። [47] “እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ፣ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?” [48] ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ፣ ጴጥሮስ ጥቂት ቀን ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ለመኑት።

ይህ የባፕቲስት ምልከታ እጅግ ግልጽ እና መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው ። ማን መጠመቅ አለበት የሚለው መፅሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል ። ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ ህፃናት መጠመቅ አለባቸውም ደግሞም መጠመቅ የለባቸውም ብሎ በግልጽ አይነግረንም ። ነገርግን ህፃናት ለድነት እና ለኃጢአት ይቅርታ ነው የሚጠመቁት ማለት *Completely Wrong* ነው ። በእርግጥ *Presbyterian* ከድነት እና ከኃጢአት ይቅርታ ጋር አያይዘው አይደለም ይህንን የሚሉት ።

## <u>እንዴት እናጥምቅ? (Mode of Baptism)</u>

ይህ ብዙም አጨቃጫቂ አጀንዳ አይመስለኝም ። በሌሎችም ዘንድ እንደ አጨቃጫቂ ተደርጎ አይታሰብም ። ይህ ቢሆንም ግን እንዴት እናጥምቅ የሚለው ላይም ልዩነት አለ ። መፅሐፍ ቅዱስ በእዚህ ጉዳይ ቃል በቃል መመሪያ አልሰጠም ። ነግርግን በዋናነት እንዴት እናጥምቅ የሚለው ላይ ሁለት ምልከታዎች አሉ ። በ *Immersion* እና በ

Sprinkle ነው ።

የ Immersionንን የሚከተሉት ባፕቲስትኦች ናቸው ። በማዝፈቅ የሚያጠምቁት ባፕቲስቶች ሲሆኑ በእዚህ ጉዳይ ላይም እጅግ አክራሪ ናቸው ። ሰዎችን ወደ ውሃ ማጥለቅ ብቸኛው የጥምቀት መንገድ ነው ብለውም ያምናሉ ። ይህ ጥምቀት በማጥለቅ ብቻ ነው የሚለው የባፕቲስትኦች አመለካከት አንድ ሰው አምኖ በመረጨት ቢጠመቅም እንኳን ድጋሚ በመዘፈቅ ወይንም በመጥለቅ ሊጠመቅ ይገባዋል የሚል አቋም አላቸው ። ባፕቲስትኦች ካቶሊኮችን ፣ ኦርቶዶክሶችን እና ሉትራንን እንደተጠመቁ አያምኑም ። ምክንያቱም ጥምቀት በመጥለቅ ስለሆነ ። ሉተርና ካልቪንም አልተጠመቁም ብለው ነው የማያምኑ ። ለእዚህም ምክንያቱ ሉተር እና ካልቪን በካቶሊክ ቤተክርስቲያን በህጻንነታቸው በመርጨት ስለተጠመቁ እና ድጋሚ በመጥለቅ ስላልተጠመቁ ነው ።

ለእዚህም እንደ ሙግት የሚያቀርቡት ባፕቲዞ የሚለው የግሪክ ቃል የተሸከመው ትርጉም ነው ይላሉ ።

 – ማርቆስ 1፥10 (አዲሱ መ.ት) ። "ከውሃው በሚወጣበትም ጊዜ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ሲወርድ አየ፤"

– ሐዋርያት 8 (አዲሱ መ.ት) ። [38] ሠረገላውም እንዲቆም አዘዘ። ከዚያም ሁለቱ አብረው ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው። [39] ከውሃውም በወጡ ጊዜ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው፤ ጃንደረባውም ከዚህ በኋላ አላየውም፤ ሆኖም ደስ እያለውም ጕዞውን ቀጠለ።

– የ Presbyterian እና የ Lutheran ምልከታ

በማጥለቅ ማጥመቅ የሚከለከል ስርአት ባይሆንም ነገር ግን ብቸኛው መንገድ እንዳልሆነም ያምናሉ ። መፅሐፍ ቅዱስ ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ስርአቶችን እንደሚያስተምርም ያምናሉ ። መርጨትንም ያካትታል ብለው ያምናሉ ። ለእዚህም የሚያቀርቡት ሙግት ባፕቲዞ የሚለው የግሪክ ቃል ማጥለቅ መዝፈቅ ተብሎ ቢተረጎምም ነገርግን ይይ የግሪክ ቃል በሌላ መንገድም ተተርጉሞ እናገኛለን ይላሉ ። ይህ ቃል መንጻት ፣ መታጠብ ተብሎም ተተርጉሟል ። ለምሳሌ ፦ ማር 7:4 ።

– ማርቆስ 7፥4 (አዲሱ መ.ት) ። "ከገበያ ሲመለሱም ታጥበው ራሳቸውን ካላነጹ በስተቀር አይበሉም ነበር። እንዲሁም ዋንጫን፣ ማሰሮን፣ ሳሕንና ዐልጋን እንደ ማጠብ ያሉትን ሌሎችን ወጎች ይጠብቁ ነበር።" በእዚህ ክፍል ባፕቲዞ የሚለው የግሪክ ቃል የአይሁድን በማፍሰስ እና በመርጨት የሚፈፀም የማንጻትን ስርአት ያመለክታል ። – ሉቃስ 11፥38 (አዲሱ መ.ት) ። "ፈሪሳዊውም ኢየሱስ ከምግብ በፊት እጁን እንዳልታጠበ ባየ ጊዜ ተደነቀ።" በእዚህም ክፍል ባፕቲዞ የሚለው የግሪክ ቃል መታጠብን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ውሏል ። ይህም የሚከናወነው እጅ ላይ ውሃን በማፍሰስ እንጂ በማጥለቅ አይደለም ። ከእዚህ በመነሳት የተሻለው የሚጥመቅ መንገድ በ Sprinkle ነው ብለው ያምናሉ ።

## <u>በማን ስም እንጠመቅ?</u>

እዚህ ርዕሰ ላይ ለክርክር እንዲቀርብ ያደረገው ምክንያት ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 28:18 ላይ ሲያዝ የነበረበት ስም እና ሐዋሪያቱ ሲያጠምቀበት የነበረበት ስም የተለያዩ በመሆኑ ነው ። – ማቴዎስ 28 (አዲሱ መ.ት) ። [18] ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ [19] ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት

አድርጓቸው፤

– ሐዋርያት ፪፥፴፰ (አዲሱ መ.ት) ። “ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ “ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።”

– ሐዋርያት ፰፥16 (አዲሱ መ.ት) ። “ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ ገና መንፈስ ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር።”

– ሐዋርያት 10፥4፰ (አዲሱ መ.ት) ። “ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው።

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ አንዳንዶች አካላትም ሆነ ቤተ እምነቶች የራሳቸውን ምልከታ ያቀርባሉ ። ለምሳሌ ፦ የሐዋርያት ስራ ምንባቦች በመያዝ *only Jesus*ኦች ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይሞግታሉ ። የማቴ ፳፰:1፱-፳ ያለውን ጥቅስ ሦስቱ ስም ለኢየሱስ የተሰጡ የክብር ስሞች እንጂ መጠሪያዎች አይደሉም እንዳልሆኑ ያስተምራሉ።

ሌሎች ደግሞ በእኛ ቤተ እምነት ውስጥ ያሉት ይህንን *problem* ለመፍታት የሚከተለውን ይላሉ ፦ ሐዋሪያቱ በኢየሱስ ስም ሲያጠምቁ የነበሩት አይሁድን ነው ኢየሱስ ደግሞ በአብ ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ያዘዘው ለአህዛብ ነው ይላሉ ። ደግሞም ለአህዛብ እና ለአይሁድ የተለያየ ስም መሆን ያስፈለገበትንም ምክንያት ያቀርባሉ ።

በሐዋርያት ሥራ በኢየሱስ ስም' የተጠመቁት ሰዎች በሥጋም ሆነ በሃይማኖት አይሁዳዊ የሆኑት ብቻ ናቸው። ይህ የሚያሳየን አይሁዳዊያን ኢየሱስን ባለመቀበላቸው ምክንያት እርሱን መቀበልና በስሙ መጠመቅ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። እነዚህ አይሁዳዊያን እግዚአብሔርን ያውቁታል።የብሉይ ኪዳኑን እግዚአብሔር እያመለኩ የሚኖሩም ናቸው።የሚቀራቸው ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ ማመን ነው።ኢየሱስ ከአባቱ ዘንድ ወጥቶ የመጣ መሆኑን እንዲሁም በእርሱ የኃጢአት ስርየት እንደሚያገኙ ማመን ስለነበረባቸው `በኢየሱስ ስም'' እንዲጠመቁ ሆኗል።

አህዛብ ግን በልዩ ልዩ የጣዖት አምልኮ ውስጥ ናቸውና እግዚአብሔርን አያመልኩትም ደግሞም አያውቁትምም ። ስለዚህ አህዛብን ስለማጥመቅ ሲነሳ ``በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ'' ስም ይጠመቁ ዘንድ የጥምቀት ቀመር ተሰጥቷል ይላሉ ። ይህንን ምልከታ ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ ይጋራዋል ። ይህንን ምለከታው **``ዐበይት መናፍቃን''** በተሰኘ ሥራው በገጽ 153-154 ጠቅሶት እንመልከት ።

ይህ በተወሰነ መጠን ጥሩ ቢሆንም ነገር ግን ለእኔ በግሌ አሳማኝ ሆኖ አላገኘሁትም ። በሁለት ምክንያቶች ። 1ኛ, በማቴዎስ ፳፰:1፱ ላይ አህዛብ ተብሎ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል *Gentile* የሚያመለክት ሳይሆን *Nations*ን የሚያመለክት ነው ። ስለዚህ አህዛብ ብቻ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይሆን ህዝቦች በሙሉ የሚጠመቁበት ስም በመሆኑ አይሁድን እና አህዛብን የሚያካትት ስም ነው ። ስለዚህ ይህ ትዕዛዝ ለ አህዛብ የሚሰራ አይደለም ።

፪ኛ, እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ማለትም ያህዌን አስቀድሞ ያውቁት ነበር ። ወልድን ማለትም ኢየሱስን ግን ስለማያውቁት በኢየሱስ ስም መጠመቅ ያስፈለጋቸው ለእዚያ ነው ። ይህ ሙግት የማያሳምነኝ ከኢየሱስ ይልቅ መንፈስን ቅዱስን ነው የማያውቁት ስለዚህ በደንብ የማያውቁት ኢየሱስን ሳይሆን መንፈስቅዱስን ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው መጠመቅ ያለቀቻው ። እንዲያውም በእዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ኢየሱስን በተሳሳተም ሆ በትክክል መንገድ ቢሆን ያውቁታል ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳን አያውቁም ነበር ። – ሐዋርያት 1፱

(አዲሱ መ.ት) ። [1] አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣ ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፤ በዚያም አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን አግኝቶ፣ [2] "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" አላቸው። እነርሱም፣ "አልተቀበልንም፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰማንም" አሉት።

– ይህ ከሆነ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ነው ማለት ምን ማለት ነው ?

በእዚያን ዘመንም ሆነ ከእዚያ ዘመን በፊት አንድ መልዕክተኛ ሲላክ የላከው አካል ማንነት እና ስልጣን የመጠየቅና የማወቅ ልማድ ነበራቸው ። ኢየሱስም ለእዚህ ነው ከፈሩሳዊ ጋር ሲነጋገር በአብዛኛው የላከኝ አብ የሚለውን ቃል በተደጋጋሚ የሚጠቀመው ። – ዮሐንስ 5፥43 (አዲሱ መ.ት) ። "እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ።"

– ዮሐንስ 10፥25 (አዲሱ መ.ት) ። "ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሳላቸው፤ "እኔ ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን አታምኑም፤ በአባቴ ስም የማደርጋቸው ታምራትም ስለ እኔ ይናገራሉ፤"

በአባቴ ስም ሲል ኢየሱስ ምድር ላይ በኖረበት ዘመን ሲጠራ የነበረበት ስም አብ የሚል አልነበረም ደግሞም ስለመጠሪያ ስም እያወራ አይደለም ። ኢየሱስ ተልዕኮውን ያገኘው ከአባቱ እንደሆነና የሚያደን ነገር የሚያደርገው ከአባቱ በተሰጠው ስልጣን እንደሆነ የሚያመለክት ነው ። ልክ እንደ ኢየሱስ ደግሞ ሐዋሪያቱም ተልከዋል ። የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመፈፀም ሲሄዱ በዘመኑ የነበሩት ማህበረሰብ ይህንን ለማድረግ ስልጣን የሰጣቸው አካል ወይንም እነርሱን የላካቸው አካል ማንነት እና ስልጣኑን ይጠይቋቸዋል ። ይህን ጊዜ ይህንን ተልዕኮ የሰጠን ፣ እንድናጠምቅ ስልጣኑን የሰጠን ኢየሱስ ነው በማለት ይናገራሉ ። ስለዚህ በኢየሱስ ስም አጠመቁ ማለት በኢየሱስ ስልጣን አጠመቁ ወይንም ኢየሱስ በሰጣቸው ስልጣን አጠመቁ ማለት ነው ።

ስም *Authority*ን የሚገልጽጹ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባትን እንመልከት ፦ ለምሳሌ ፦ – ዮሐንስ 2 (አዲሱ መ.ት) [18] አይሁድም፣ "ይህን ሁሉ ለማድረግ ሥልጣን እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን ታምራዊ ምልክት ታሳየናለህ?" አሉት። [19] ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ" ብሎ መለሰላቸው። [20] አይሁድም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤ ታዲያ አንተ እንዴት በሦስት ቀን መልሰህ ታነሣዋለህ?" አሉት። [21] ቤተ መቅደስ ሲል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር። [22] ከሙታንም ከተነሣ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደ ተናገረ አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና ኢየሱስ ያለውንም ቃል አመኑ። [23] በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ብዙ ሰዎች ያደረገውን ታምራት አይተው በስሙ አመኑ፤ይህንን አይነት ትርጉ 1954ቱ ላይ አናገኝም ነገርግን አዲሱ መደበኛ ትርጉም ላይ እና የኢንግሊዘኛ ትርጉሞች ላይ እናገኛለን ። ለምሳሌ *NIV.* ። *18 The Jews then responded to him, "What sign can you show us to prove your authority to do all this?"..... 23 Now while he was in Jerusalem at the Passover Festival, many people saw the signs he was performing and believed in his name.* በተጨማሪም ፦ በሐዋሪያት ስራ ላይ ይህንን እናገኛለን ። "እነርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከል አቁመው፣ "ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይል ወይም በማን ስም ነው?" ብለው ጠየቋቸው።" – ሐዋርያት 4፥7 (አዲሱ መ.ት) ። ስለዚህ በዘመኑ የነበረው ማህበረሰብ ስምን የሚረዱበት መንገድ ከ ስልጣን ጋር አያይዘውት ነው ። *only Jesus*ኦች ሶስት አካላት እንዳሉ ስለሚክዱ ነው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ የማይፈልጉት ።

**በወንድም ተካልኝ ኀ/ሚካኤል**